# ሚሪያም ማኬባ

ባለፈው እሁድ እ.አ.ቁ. ህዳር 8 ቅን 2008 ዓ/ም በ76 ዓመቷ ድንገት በልብ ድካም ያረፈቸው ማሪያ ማኬባ (አለያም ማማ አፍሪቃ) ደቡብ ጣሊያን በሚገኘው ኮስቴል ቮልቱርኖ በሚባለው አገር የዘፈን ትዕይንቷን ካሳየች በኋላ መሆኑ ተዘግቧል።

ዜንሲ ሚሪያም ማኬባ እ.አ.ቁ. መጋቢት 4 ቀን 1932 ዓ/ም ፕሮስፔክት በሚባለው ከዮሐንስቦርግ ወጣ ብሎ ከሚገኘው ከተማ ተወለደች። አባቷ አስተማሪ እናቷ የቤት አገልጋይ (ገረድ) ስትሆን ሁለቱም የሆሳ ነገዶች ናቸው። በማስታወሻዋ እንደገለጸችው ዘመድ አዝማድ ድምጿን ከናይታንግል ጋር እያወዳደሩ እንድትዘፍን ያበረታቷት እንደነበር አትታለች። ትምህርቷን የተከታተለችው ፕሪቶሪያ በሚገኘው የሜተዲስት ቤ/ክርስቲያን ነበር። እዚሁ ት/ቤት እያለች የእንግሊዝ ንጉስ የነበረው ጎርጊስ 6ኛ ደቡብ አፍሪካን ሲጎበኝ እፊቱ ቀርባ ተጫውታለች። በነጮች ቤት በግርድና በምታገለግልቤት ጊዜ በየሰርጉ እና በየልቅሶ ቤቱ ታንጎራጉር እንደነበር ታሪኳ ይናገራል። አለም አቀፍ ዝናን ያገኘችው እ.አ.ቁ. በ1959 ጸረ ዘረኝንት ላይ ባተኮረው ተመለሽ አፍሪቃ(Come Back, Africa) በተባለው ስነድ መሪ ተዋናይ ሆና በመስራቷ ነበር። ይህን ባሳየች ባመቱ ለናቷ ቀብር ለመድረስ ስትመለስ ፓስፖርቷ መሰረዙ እና የዜግነት መብቷ መገፈፉን የሰማቸው ። ይህ በሆነ በ30 አመት በኋላ በማንዴላ ጥሪ ነው ላገሯ የበቃችው።

ኋላ ጥቁር ማንሀታን በመባል የሚታወቁ ሙያተኛ የሙዚቃ ቡድን ተቀላቅላ በደቡብ አፍሪቃ፣ ዚምባቡዌ (የቀድሞው ሮዴሺያ) እና በኮንጎ እየዞረች ታሳይ ነበር። በዚሁ ከላይ በተጠቀስው ዓመተ ምህረት ኪንግ ኮንግ እየተባለ በሚጠራው የጃዝ ኦፔራ ተዋናይ ሆና ዓለምን ዞራለች። እ.አ.ቁ. ብ1963 ዓ/ም በተ/መ/ የዘረኛ ጉዳይ ልዩ ደርግ ፊት በመቅረብ በዘረኛው መንግስት ላይ ለሚያሳልፈው ዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ቃሏን ሰጥታለች። ይህን በማድረጓም ዘረኛው መንግስት ዘፈኖቿን በሙሉ አግዷል።

ይህ ለሰው ልጅ መብት መቆም እና ድምፀ መረዋነቷ በመንግስታት መሪዎችም ፊት አቅርቧታል። ለሁለተኛ ጊዜ በ1962 ዓ/ም ያሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበረው ኬኔዲ ልደቱን ሲያከብር እፊቱ በመዝፈን አክብራለታለች። ኋላ ግን ስቶክሊ ካርሚካኤል የተባለውን የጥቁር ሀይል አቀንቃኝ በማግባቷ ውለታ አሳጥቷት በባለ ስልጣናቱ ውከባ አሜሪካንን ለቃ ጊኒ ተሰዳለች። በሙያዋ ያገሯን ጭቆናና የዘረኛውን አገዛዝ በማጋለጥና በማውገዝ ባሜሪካ፣ በአውሮፓና በሌላው ዓለም የዘፈን ትዕይንት ስታሳይ ሶስት አስርታት አሳልፋለች።

ይህ ታሪኳ በየቦታው ተተንትኖ ይገኛል። እኔ ማስታወስ የምፈልገው በደንብ ያልታወቀውን እና ሰፋ ያለ ትንተና ያለተሰጠውን ነው።  ይኼውም አገሬ ያረገችውን ነው። አዎ በኢትዮጵያ። የአዲስ አበባ ሒልተን ሆቴል ሲመረቅ የጥንቱ ትዝ አለኝ የሚለውን ዘፈን ባማርኛ ዘፍናለች። ይህ ዘፈኗ አልፎ አልፎ በኢትዮጵያ ራዲዮ በእንግሊዝኛው መርሀ ግብር ይተላለፍ ነበር። ይህ ቴፕ አይጠፋም እና ያገኘ ወይ ያለው ቢያሰማን እጅግ መታደል ነው። ከታሪክ ስነድነቱ ተጨማሪ የሙዚቃው ቃና ቅንብሩ፣ የዜማው አወራረድ እና ረድፋዊ ይዘቱ ታላቅ አፍሪቃዊ ቅላጼ ነው። እግረ መንገዳችሁንም ማን እንደ አቀናበረው ብታሳውቁን በማለት ለራዲዮ ጣቢያዎች፣ ለቴሌቪዥን አውታሮች እንዲያው በጠቅላላ ዜና ስርጭቶች ፈልፍለው ላድማጭ ቢያቀርቡት ብዬ እማጸናለሁ።

በቸር ይግጠመን
ክንፈ ሚካኤል
ህዳር ፲ቀን ፳፻፰ ዓ.ም.